Amharic / አማርኛ

# መብትዎን ይወቁ፣ ሃሳብዎን ይግለጡ

**መስከረም/September 2023 ዓ›ም**

በማንም ተጽእኖ የለለበት ነጻ የአእምሮ ጤና ውክልና/ Independent Mental Health Advocacy (IMHA) መብትዎን እንዲያውቁ እና ሀሳብዎን እንዲገልጹ ሊረዳዎት ይችላል። IMHA ነጻ እና ምስጢራዊ የጥብቅና አገልግሎት ሲሆን፣ አገልግቱን የሚያገኙት፡

- የግዴታ ህክምና እየተደረገላቸው ላሉት
- ወይም የግዴታ ህክምና ማግኘት ለሚያስጨንቃቸው ይሆናል።

IMHA በቪክቶሪያ ሊጋል ኤይድ የሚሰጥ አገልግሎት ቢሆንም የህግ አገልግሎት አይደለም። IMHA ነፃ የሆነ እና ከአእምሮ ጤና የተለየ አገልግሎት ነው።

## እናነጋግርዎታለን

ከመስከረም 1 ቀን 2023 ዓ.ም ጀምሮ *የአእምሮ ጤናና ደህንነት ደንብ 2022 (ቪክ)*/Mental Health and Wellbeing Act 2022 (Vic) እንደሚለው የግዴታ ህክምና በምታደርጉበት ጊዜ ቁልፍ ነጥቦችን ለእኛ እንደሚገልጹልን በግልጽ ተቀምጧል። ስለ 'IMHA መቼ እንደሚገለጽለት/'When will IMHA be notified?' ተጨማሪ ይወቁ በዚህ ሰነድ ክፍል።

እንዳናናግርዎ ካልነገሩን በስተቀር እናነጋግርዎትአለን። ከእርስዎ ጋር ስንገናኝ ምን እንደምናደርግ እናስረዳዎትአለን፤ እንዲሁም የእኛን አገልግሎቶች ማግኘት የሚፈልጉ ከሆነ መወሰን ይችላሉ። እንዳናናግርዎ ከፈለጉ ለመናገር የዚህን ወረቀት ክፍል 'እንዳንገናኝዎት ይንገሩን' የሚለውን ይመልከቱ።

## እርስዎ እኛን ማነጋገር ይችላሉ

በአሁኑ ጊዜ የግዴታ ህክምና የማያካሂዱ ከሆነ፣ ነገር ግን የግዴታ ህክምናውን ለማግኘት የሚጨነቁ ከሆነ፣ አሁንም የ IMHA አገልግሎት ማግኘት ይችላሉ። ሰለጉዳዩ ስለማይነገረን እኛን በቀጥታ እንዲያነጋግሩን ይገባል። በስልክ 1300 947 820 መደወል ይችላሉ። ድረ ገጻችንን www.imha.vic.gov.au ይጎብኙ ወይም ኢሜይል imhacontact@imha.vic.gov.au ይላኩልን።

ሰዎች የግዴታ ህክምና ስለመቀበል ሊጨነቁ የሚችሉባቸው የተለመዱ ምክንያቶች፣ ከህክምና አድራጊ ቡድን ጋር መቃረን እንደማይችሉ፣ ወይም የህክምና ቡድንዎ አንድ ነገር የማያደርጉ ከሆነ የበግዴታ ህክምና እንዲያደርጉ እንደሚያስገድዱዎ መጥቀሳቸውን ያካትታል።

## IMHA እንዴት ሊረዳዎ እንደሚችል

በሚከተሉት መንገዶች እንረዳዎትአለን፡

- የግምገማዎን፣ የህክምናዎን፤ የእንክብካቤዎ እና የማገገም መረጃዎችን እንዲረዱ መርዳት
- የግምገማዎን፤ ህክምናዎን እና እንክብካቤ በተመለከተ ውሳኔዎች ስለማድረግ
- መብትዎን መረዳትና መጠቀም
- ምርጫዎችን አስቀድመው ማቅረብ/መግለጥ
- የመረጡትን የድጋፍ ሰጪ ሰው መሾም
- ሁለተኛ የስነ-አእምሮ ሙያተኛ ማግኘት
- የህግ ምክር መጠየቅ
- ለአዕምሮ ጤና ልዩ ፍርድ ቤት (Mental Health Tribunal) ማመልከት
- የአዕምሮ ጤናንእና የደህንነት አገልግሎት ስርአትን መረዳትና ማግኘት
- ውሳኔዎን፤ አመለካከትዎን እና ምርጫዎን ለአዕምሮ ጤና እና ደህንነት አገልግሎት እና ለሌሎችም መግለጽ
- ቅሬታ ማቅረብ ናቸው።

አስተርጓሚ ማዘጋጀት እንችላለን። በተጨማሪም በ 131 450 የትርጉምና የትርጁማን አገልግሎት ስልክ ደውለው ከእኛ ጋር እንዲያገናኙዎት መጠየቅ ይችላሉ።

IMHA በእርስዎ ፈቃድ ስለ አዕምሮ ጤና እና ደህንነት አገልግሎት ያለዎትን አመለካከት ወክሎ መናገር ይችላል።

የእርስዎ IMHA አቡካቶ፡

- በእርስዎ መመሪያ መሰረት እርምጃ መውሰድ
- ያለ ፈቃድዎ እርምጃ አንወስድም
- ቢያንስ እድሜዎ 16 ዓመት ከሆነ፣ ሌሎች እርስዎን በጣም ይጠጥቅማል ብለው በሚያስቡት ነገር አይመራም። ድሜዎ 15 ዓመት ወይም ከዚያ በታች ከሆነ IMHA የእርስዎን አመለካከት እንደሚያበረታታ እና የእርስዎን ጥቅም ለመጠበቅ ከእርስዎ፤ ቤተሰቦችዎ፤ ተንከባካቢዎችዎ እና ደጋፊዎችዎ ጋር አብሮ ይሰራል።

## እንዳንገናኝዎት ከፈለጉ ይንገሩን

በሚከተሉት ጉዳዮች ላይ እርግጠኛ እንድንሆን፣ ስለ እርስዎየመለያ መረጃ ማቅረብ ይኖርብዎታል፡

- ከእርስዎ ጋር መገናኘት እንዳንሞክር፣ እና
- ስለ አስገዳጅ ህክምናዎ ያገኘነውን መረጃ እንድሰርዝ።

የሚሰጡን መረጃ በአስተዳደር ሰራተኞቻችን በኩል ይያዛል። የግል መረጃዎችን እንዴት እንደምንይዝና የግል ሚስጥርዎን እንደምንጠብቅ ለማወቅ በድረገጽ www.imha.vic.gov.au/how-we-handle-personal-information ላይ ማየት ይችላሉ።

እንዳንገናኝዎት ለመናገር፡

- በስልክ ጥሪ 03 9093 3701
- ቅጹን ለመሙላት ድረገጽ www.imha.vic.gov.au/optout ይጎብኙ
- የሚከተለውን ቅጽ አጠናቅቀው በኢሜል imhaadmin@imha.vic.gov.au ወይም በፖስታ አማካኝነት ይላኩ።

Independent Mental Health Advocacy

ፖ.ሳ.ቁጥር/GPO Box 4380

Melbourne VIC 3001

- በሚከተለው የስምምነት ጽሁፋዊ መግለጫ እና መረጃ ጋር አድርገው በኢሜል imhaadmin@imha.vic.gov.au ይላኩልን።

ቅጹን ሞልተው ለማቅረብ የሚረዳዎ ሠራተኛ ወይም ደጋፊ ሰጪ መጠየቅ ይችላሉ።

እኔ, ______________________________ በግዴታ ህክምና ትእዛዝ ወይም በሌላ በማንኛውም በተቀመጡት ቁልፍ ነጥቦች ላይ IMHA እንዲያነጋግረኝ አልፈልግም። ስለ አስገዳጅ ህክምናዬ IMHA ወደፊት የሚቀበለው ማንኛውም መረጃ እንደሚሰረዝ ተረድቻለሁ።

የትውልድ ቀን፡ ____________________

ፊርማ፡ ____________________

ቀን፡-፡ ____________________

የአገር አቀፍ የ UR ቁጥር (SWURN)፡ ____________________

ይህ ቁጥር ለህዝብ መገልገያ የተመደበውን የአእምሮ ጤና አገልግሎት የሚያገኙ ተጠቃሚዎች በሙሉ የሚመደብ ልዩ ቁጥር ነው። ይህን ቁጥር እርስዎን በትክክል ለይተን ለማወቅ እንድንችል እንጠቀማለን። የእርስዎን SWURN ካላወቁት የአእምሮ ጤናን እና ደህንነት አገልግሎት መጠየቅ ወይም ማን መጠየቅ እንዳለብዎ መረጃ ለማግኘት IMHA መደወል ይችላሉ።

የስልክ ቁጥር: ______________________

ኢሜይል: ______________________

አድራሻ: ______________________

ሰፈር/ከተማ: ______________________

የፖስታ ኮድ: ______________________

ሀሳብዎን ቆይተው ከቀየሩ የግዴታ ህክምና ሲደረግልዎ እና IMHA እንዲያነጋግርዎ የሚፈልጉ ከሆነ እንዲህ ማድረግ ይችላሉ፡

- በስልክ 1300 947 820 ይደውሉ
- በ imhacontact@imha.vic.gov.au ኢሜል ያድርጉ
- ድረገጻችንን www.imha.vic.gov.au ይጎብኙ

## ለIMHA መቼ ነው የሚነገር?

IMHA እንዲህ ከሆነ ይነገራል፡

- በጊዜያዊ የህክምና ትእዛዝ ወይም በህክምና ትእዛዝ ላይ ተቀምጠው ከሆነ፣ ይህም በህክምና ማጣሪያ ወይም የደህንነት ታማሚ መሆንን ጨምሮ
- በንግግር የመግባባት መብትዎ ከተገደበ
- ጊዜያዊ የህክምና ትእዛዝዎ ወይም የህክምና ትእዛዝዎ ከህብረተሰቡ ወደ የሆስፒታል ታካሚነት ወይም ከሆስፒታል ታካሚነት ወደ ማህበረሰብ ተቀይሮ ከሆነ
- ጊዜያዊ የህክምና ትእዛዝዎ ወይም የህክምና ስርዓትዎ ከተከለከለ ወይም ከተሰረዘ
- የአዕምሮ ጤና ልዩ ፍርድ ቤት የክርክር ቀጠሮ ካለዎት
- የገደብ ጣልቃ ገብነት ጥቅም ላይ ይውላል፣ ለምሳሌ፡ እንዲገለሉ ከተደረገ ወይም በአካል ወይም በኬሚካል ታግተው ከሆነ
- የዝውውር ተእዛዝዎ ለህክምና ወደ ሌላ የአእምሮ ጤና አገልግሎት ሄደው እንዲታከሙ ተቀይሮ ከሆነ ነው።

የደህንነት ታማሚ ከሆኑ IMHA ሊነግርዎት የሚችለው፡

- የተመደበ የአእምሮ ጤና አገልግሎት ለህክምና ከተቀበለዎት ወይም ወደዚያ ከተዳዙ
- ወደ እስር ቤት እንዲመለሱ ከሆስፒታል ከወጡ።

የህክምና ምርመራ ታካሚ ከሆኑ IMHA ሊነረው የሚችለው፡

- ወደ ተወሰነ የአዕምሮ ጤና አገልግሎት ከተዳዙ፣ የምርመራ ፎረንሲክ ፈቃድ ፓነል/ቡድን (Forensic Leave Panel) መዳዛዝዎን ካጸደቀ ወይም በሌላ መንገድ በተፈቀደለት አካል መመሪያ ከተሰጠ ይሆናል
- የስነ አእምሮ ሀኪምዎ ወይም ዋናው የስነ አእምሮ ሀኪም ወደ ሌላ የተመደበ የአእምሮ ጤና አገልግሎት እንዲዳዙ መመሪያ ከሰጠ
- ፎረንሲካሬ (Forensicare) ለአእምሮ ልዩ ጤና ፍርድ ቤት (Mental Health Tribunal) ከፍተኛ ክትትል የሚደረግበት ትእዛዝ፣ ይህ ትእዛዝ ከተላለፈና መቼ እንደሆነ ሲመለከት ይሆናል።

## IMHAን እንዴት ማነጋገር እና ተጨማሪ መረጃ ማግኘት እንደሚቻል

- ድረገጻችንን www.imha.vic.gov.au ይጎብኙ ወይም በኢሜል imhacontact@imha.vic.gov.au ይላኩ
- ለIMHA በስልክ ቁጥር 1300 947 820 ይደውሉ። ይህም IMHA ወኪል ሰራተኛ ከጥዋቱ 9:30 am እስከ ከሰዓት በኋላ 4:30 pm በሳምንት ሰባት ቀናት (ከህዝባዊ በዓላት በስተቀር) ይገኛሉ።
- ስለ መብትዎ የድምጽ ቅጂ ለመስማት በስልክ 1800 959 353 ላይ ለIMHA መብት መስመር ይደውሉ።
- IMHAን ለማነጋገር እንዲረዳዎት የአእምሮ ጤና አገልግሎት ሰጪ፣ ተንከባካቢ ወይም ሌላ ድጋፍ ሰጪን ይጠይቁ።
- ስለ IMHA አስተያየት መስጠት ወይም ቅሬታ ማቅረብ የሚፈልጉ ከሆነ፣ እባክዎ ያነጋግሩን ወይም የድረ ገጻችንን አስተያየት መስጫ ክፍል ይጎብኙ።
- 131 450 በመደወል ነጻ አስተርጓሚ ማግኘት፤ ከዚያም በ1300 947 820 ለእኛ እንዲደውሉልን መጠየቅ።